አንዳችሁ ሰዎች ሰጡትም ከለከሉት ሰዎችን ከሚለምን ይልቅ ገመዱን ይዞ በጀርባው እንጨት አስሮ እያመጣ በመሸጥ አላህ ፊቱን (ከመገረፍ) ቢጠብቅለት የተሻለ ነው።

ከዙበይር ቢን አልዓዋም -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው: ነቢዩ - የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ
ይስፈንና - እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ ሰዎች ሰጡትም ከለከሉት ሰዎችን ከሚለምን ይልቅ ገመዱን ይዞ በጀርባው እንጨት አስሮ እያመጣ በመሸጥ አላህ ፊቱን (ከመገረፍ) ቢጠብቅለት የተሻለ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

ነቢዩ - የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና - ሰው ማንኛውንም ስራ መስራት እንዳለበትና ገመዱን ይዞ ጀርባው ላይ የሚሸከመውን እንጨት ሰብስቦ በገመዱ አስሮ በመሸጥ ካገኘው ገንዘብም መመገቡ ወይም መመፅወቱ ከሰዎችም መብቃቃቱና ከልመና ውርደት (በሰው ፊት ከመገረፍ) ፊቱን መጠበቁ ሰጡትም ከለከሉትም ሰዎችን ከመለመን የተሻለ እንደሆነ ገለፁ። ሰዎችን መለመን ውርደት ነው። አማኝ ደግሞ ቆፍጣና እንጂ ወራዳ አይደለም።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3785